## የገንዘብ ሚኒስቴር

# ከገቢ ግብር ነፃ የተደረጉ ገቢዎች
# አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 200/2013

መጋቢት 2011 ዓ/ም
አዲስ አበባ

## ከገቢ ግብር ነፃ የተደረጉ ገቢዎች አፈጻጸም

# መመሪያ ቁጥር 200/2013

## 1. አወጫጭ ባለሥልጣን

የገንዘብ ሚኒስትሩ በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 አንቀጽ 65/1/ሀ እና አንቀጽ 99/2/ በተሰጠው ሥልጣን መሰረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

## 2. አጭር ርእስ

ይህ መመሪያ ከገቢ ግብር ነፃ የተደረጉ ገቢዎች አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 200/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 3. ትርጓሜ

በፌደራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 ወይም በፌደራል የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 ትርጉም የተሰጠው ቃል በዚህ መመሪያ ወስጥ ጥቅም ላይ የዋለ እንደሆነ በታክስ አስተዳደር አዋጁ ወይም በገቢ ግብር አዋጁ የተሰጠዉን ትርጉም ይይዛል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ወስጥ ፡-

ሀ. **"ደመወዝ"** ማለት በአንድ የስራ ደረጃ ላይ የተመደቡ ሠራተኞች ለሚሰጡት አገልግሎት በቀጣሪው የሚከፈል ክፍያ ሲሆን አበል እና ጥቅማ ጥቅሞችን አይጨምርም፡፡

ለ. **"የትራንስፖርት አበል"** ማለት በቀጣሪው እና በተቀጣሪው መካከል በተደረገ ዉል ወስጥ በግልጽ የተመለከተ እና ተቀጣሪው ከመኖሪያ ቤቱ ወደ ሥራ እንዲሁም ከሥራ ቦታው ወደ መኖሪያ ቤቱ ለመጓጓዝ እንዲሁም ተቀጣሪው ሥራዉን ለማከናወን መደበኛ የሥራ ቦታው በሚገኝበት ከተማ ወስጥ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ለመዘዋወር የሚያስፈልገው የትራንስፖርት ወጪ ለመሸፈን በቀጣሪው የሚከፈል አበል ነው፡፡

ሐ. **"የውሎ አበል"** ማለት አንድ ተቀጣሪ የተቀጠረበትን ሥራ ለማከናወን መደበኛ የሥራ ቦታው ከሚገኝበት ከተማ ወጪ ከ25 ኪሎ ሜትር በላይ ርቆ በሚሄደበት ጊዜ ለመኝታ፣ ለምግብ፣ ለመጠጥና ለተዛማጅ ወጪዎች የሚከፈል አበል ነው፡፡

መ. **"በሥራ ሁኔታ አስቸጋሪነት ምክንያት የሚከፈል አበል"** ማለት የሥራ ሁኔታው ለጨረር፣ ለበሽታ፣ ለኬሚካል ልቀት ወይም ብክለት፣ ለንፁህ አየር እጥረት፣ ለከፍተኛ ሙቀት፣ ለከፍተኛ ቅዝቃዜ የሚያጋልጥ ወይም በሚፕቸውም ሌላ ምክንያት በተቀጣሪው ጤና ደህንነት ላይ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል መሆኑን ከግምት ወስጥ በማስገባት የሚከፈል አበል ነው፡፡

ሠ. **"በሥራ ቦታው አስቸጋሪነት ምክንያት የሚከፈል አበል"** ማለት የሥራ ቦታው የሚገኝበት ከተማ ከፍተኛ ሙቀት ያለው ወይም ለኑሮ አስቸጋሪ በመሆኑ ወይም በሌላ ተመሳሳይ ምክንያት

በተቀጣሪው ላይ ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት ከግምት ወስጥ በማስገባት የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ባወጣው መመሪያ መሠረት የሚከፈል አበል ነው፡፡

ረ. "አዋጅ" ማለት የፌደራል የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 ነው፡፡

ሰ. "ደንብ" ማለት የፌደራል የገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 410/2009 ነው፡፡

ሸ. "ባለሥልጣን" ማለት የገቢዎች ሚኒስቴር ወይም የአዲስ አበባ ወይም የድሬዳዋ አስተዳደር ገቢዎች ባለስልጣን ነው፡፡

## 4. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በአዋጁ እና በደንቡ ከገቢ ግብር ነፃ በተደረጉ ገቢዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት
## አበል እና ሽልማት ከግብር ነፃ የሚደረግበት ሁኔታ

## 5. የትራንስፖርት አበል እና የማጓጓዣ ወጪ

1. በስራ ባህሪው ምክንያት ሥራውን ከቦታ ወደቦታ በማዘዋወር የሚያከናውን ተቀጣሪ ለአንድ ወር ጉዞ የሚከፈለው የትራንስፖርት አበል ከገቢ ግብር ነፃ የሚደረገው ከጠቅላላ የወር ደመወዙ ከአንድ አራተኛ (1/4) ባልበለጠ ማጠን ብቻ ነው፡ ይሁንና የተቀጣሪው ጠቅላላ የወር ደመወዝ አንድ አራተኛ ከብር 2200 የሚበልጥ ሲሆን ከግብር ነፃ የሚደረገው የትራንስፖርት አበል በማንኛውም ሁኔታ ከብር 2200 ሊበልጥ አይችልም፡፡

2. አንድ ተቀጣሪ በስራ ባህሪው ምክንያት በማዘዋወር ለሚሰራው ስራ ለነዳጅ ወጪ የሚከፈለው ጥሬ ገንዘብ ለትራንስፖርት አበል እንደተከፈለ ተቆጥሮ ከገቢ ግብር ነጻ የሚደረገው ከጠቅላላ የወር ደመወዙ ከአንድ አራተኛ (1/4) ባልበለጠ ማጠን ብቻ ነው፡ ይሁንና የተቀጣሪው ጠቅላላ የወር ደመወዝ አንድ አራተኛ ከብር 2200 የሚበልጥ ሲሆን ከግብር ነፃ የሚደረገው የነዳጅ ወጪ በማንኛውም ሁኔታ ከብር 2200 ሊበልጥ አይችልም፡፡

3. አንድ ተቀጣሪ ከመኖሪያ ቤቱ ወደ ስራው ቦታ እንዲሁም ከስራው ቦታ ወደ መኖሪያ ቤቱ የሚጓጓዝበት የመሥሪያ ቤቱ የትራንስፖርት ሰርቪስ ቢቀርብም ባይቀርብም ለዚህ ዓይነቱ የትራንስፖርት አበል ከገቢ ግብር ነፃ የሚደረገው ከብር 600 ባልበለጠ ማጠን ብቻ ነው፡፡

4. አንድ ተቀጣሪ ከመኖሪያ ቤቱ ወደ ስራው ቦታው እንዲሁም ከስራው ቦታ ወደ መኖሪያ ቤቱ ለመሄድ ለነዳጅ ወጪ በጥሬ ገንዘብ የሚከፈለው የትራንስፖርት አበል ከገቢ ግብር ነፃ የሚደረገው ከብር 600 ባልበለጠ ማጠን ብቻ ነው፡፡

5. አንድ ተቀጣሪ ሥራውን ለማከናወን መደበኛ የሥራ ቦታው ከሚገኝበት ከተማ ወጪ ሲንቀሳቀስ ለማጓጓዣ ወጪ የሚሰጠው ክፍያ ከግብር ነፃ ሊሆን የሚችለው በስራ ላይ ባለው የትራንስፖርት ታሪፍ ወይም በሚቀርበው ማስረጃ ላይ የተመሰረተ ሆኖ ከከፈለው የአየር፣ የውሃ እና የየብስ ትራንስፖርት የአገልግሎት ዋጋ ሊበልጥ አይችልም፡፡

6. አንድ የውጭ አገር ዜጋ ሥራን ለማከናወን ወደኢትዮጵያ ሲመጣ እና የወል ዘሙን ጨርሶ ከሀገር ሲወጣ የሚከፈለው የትራንስፖርት ወጪ ከግብር ነፃ ሊሆን የሚችለው በተፈጸመው የቅጥር ውል ማስረት እና የአየር፣ የውሃ እና የየብስ ትራንስፖርት አገልግሎት ዋጋ ታሪፍ መሠረት ሆኖ ከግብር ነፃ የሚሆነው ለግል መገልገያ ዕቃዎቹ የሚከፈለው የጭነት ሂሳብ ከ300 ኪሎ ግራም ሊበልጥ አይችልም፡፡

7. አንድ ግብር ከፋይ ከመደበኛ መኖሪያ ቦታቸው ርቀው ሥራቸውን የሚያከናወኑ ሠራተኞች ቤተሰባቸውን ለማጠየቅ የሚያደርጉትን ጉዞ ወጪ የሚሸፍን በሚሆንበት ጊዜ የዚህ ዓይነቱ ወጪ ከግብር ነፃ ሊሆን የሚችለው በተፈፀመው የቅጥር ውል ውስጥ ቀጣሪው ይህ ግዴታ ያለበት ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡ ሆኖም ለዚህ ዓይነቱ ጉዞ የሚከፈለው ወጪ ከግብር ነፃ የሚደረገው በአንድ የግብር ዓመት ከሁለት የደርሶ መልስ ጉዞ ባልበለጠ ማጠን ብቻ ነው፡፡

## 6. የወሎ አበል፣

1. በሀገር ውስጥ ለሚደረጉ ጉዞዎች የሚከፈል የወሎ አበል፣

ሀ. አንድ ተቀጣሪ የሚከፈለው የቀን የወሎ አበል ከገቢ ግብር ነፃ የሚደረገው ከብር 500 ወይም ከደሞዙ 4% ከሁለቱ ከፍተኛ ከሆነው ማጠን ባልበለጠ ብቻ ነው፡፡

ለ. ለዚህ ንኡስ አንቀጽ ለፊደል ተራ ሀ አፈጻጸም አንድ ተቀጣሪ የአልጋ አበል ያለገደብ ወይም በተወሰነ ገደብ በደረሰኝ የሚወራረድለት ከሆነ በደረሰኙ መሠረት ለአልጋ የተከፈለው ገንዘብ ከግብር ነፃ የሚደረግ ሲሆን ለቁርስ፣ምሳ፣ እራት እና የመሳሰሉ ወጪዎች የሚሰጠው የወሎ አበል ከግብር ነጻ ሊደረግ የሚችለው ከብር 300 ወይም ከደሞዙ 2.5% ከሁለቱ ከፍተኛ ከሆነው ማጠን ባልበለጠ ብቻ ነው፡፡

ሐ. ለማናቸውም ድርጅት ስራ አስኪያጅ ወይም ምክትል ስራ አስኪያጅ የሚከፈለው የወሎ አበል ከግብር ነፃ የሚደረገው ከብር 1000 ወይም ከወርሓዊ ደሞዙ 5 በመቶ ከፍተኛ ከሆነው ማጠን ባልበለጠ ብቻ ነው፡፡

መ. ለዚህ ንኡስ አንቀጽ ለፊደል ተራ ሐ አፈጻጸም አንድ ስራ አስኪያጅ ወይም ምክትል ስራ አስኪያጅ የአልጋ አበል ያለገደብ ወይም በተወሰነ ገደብ በደረሰኝ የሚወራረድለት ከሆነ በደረሰኙ መሠረት ለአልጋ የተከፈለው ገንዘብ ከግብር ነፃ የሚደረግ ሲሆን፣ ለቁርስ፣ ምሳ፣ እራት እና ለመሳሰሉ ወጪዎች የሚሰጠው የወሎ አበል ከገቢ ግብር ነጻ የሚደረገው ከብር 600 ወይም ከወርሓዊ ደሞዙ 3 በመቶ ከፍተኛ ከሆነው ማጠን ባልበለጠ ማጠን ብቻ ነው፡፡

2. ወደ ወጪ ሀገር ለሚደረጉ ጉዞዎች የሚከፈል የወሎ አበል፣

ሀ. አንድ ተቀጣሪ የተቀጠረበትን ስራ ለማከናወን ወደ ውጭ ሀገር ለሚያደርገው ጉዞ የሚከፈለው የወሎ አበል ከገቢ ግብር ነጻ የሚደረገው መንግስት ከተሿሚዎች ወጪ ለሌሎች ተቀጣሪዎቹ ከወሰነው የወሎ አበል ልክ ባልበለጠ ብቻ ነው፡፡

ለ. የማናቸውም ድርጅት ሥራ አስኪያጅ ወይም ምክትል ሥራ አስኪያጅ ከድርጅቱ ስራ ጋር በተገናኘ ወደ ውጭ ሀገር ለሚያደርገው ጉዞ የሚከፈለው የወሎ አበል ከገቢ ግብር ነጻ

የሚደረገው ማግስት ከተሿሚዎች ወጪ ለሌሎች ተቀጣሪዎቹ በወሰነው የወሎ አበል ልክ ላይ 20 በመቶ ተጨምሮበት ይሆናል፡፡

3. የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ ቢኖርም በሀገር ወስጥ ለሚደረግ የስራ እንቅስቃሴ የኮንስትራክሽን ማሽነሪ ኦፕሬተሮች የሚከፈል የወሎ አበል ከ25 ኪ.ሜ ባነሰ ወይም በበለጠ ርቀት ቢሆንም የተከፈለው የወሎ አበል ከግብር ነፃ ይሆናል፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 እና 3 የተደነገገው ቢኖርም የማግስት ማስሪያ ቤት ለተሻሚዎች እና ለተቀጣሪዎቻቸው ከመደበኛ የስራ ቦታቸው ወጪ ከ25 ከሎሜትር በላይ ርቀው በመሄድ ለሚያከናወኑት ስራ የሚከፍሉት የቀን ወሎ አበል ሙሉ በሙሉ ከግብር ነፃ ተደርጓል፡፡

5. ለዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 5 አፈፃፀም፦

   1. "የማግስት ማስሪያ ቤት" የሚለው ሀረግ በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ የተሰጠዉን ትርጉም ይይዛል፡፡

   2. 25 ኪሎ ሜትር የሚለካው ከከተማው አስተዳደር ማዘጋጃ ቤት ወሰን ጀምሮ ሲሆን ማዘጋጃ ቤት የሌለው ከሆነ እንደ የሁኔታው ከከተማ አስተዳደር ወይም ከቀበሌ አስተዳደር ወሰን ጀምሮ ተቀጣሪው እስከሚጓዝበት ቦታ ድረስ ያለው ርቀት ነው፡፡

## 7. በስራ ቦታው አስቸጋሪነት ምክንያት ለተቀጣሪ የሚከፈል አበል

1. በስራ ቦታው አስቸጋሪነት ምክንያት የሚከፈል አበል ከግብር ነፃ ሊሆን የሚችለው የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ባወጣው መመሪያ የዚህ ዓይነቱ አበል እንዲከፈልባቸው ለተፈቀደ አካባቢዎች እና ከሚፈቀደው የአበል ማጠን ያልበለጠ ይሆናል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 የተደነገገው በሲቪል ሰርቪስ አዋጅ ለሚተዳደር የማግስት ማስርያ ቤት፣ የማግስት የልማት ድርጅት፣ ማግስታዊ ያልሆነ ድርጅት፣ የግል ድርጅት ተቀጣሪ ወይም ሌላ ማንኛዉም ተቀጣሪ ወይም ተሿሚ በሥራ ቦታው አስቸጋሪነት ምክንያት የሚከፈል አበል ላይ በተመሳሳይነት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## 8. በስራ ሁኔታው አስቸጋሪነት ምክንያት ለተቀጣሪ የሚከፈል አበል

1. በሥራ ሁኔታ አስቸጋሪነት ምክንያት የሚከፈል አበል ከግብር ነፃ ሊሆን የሚችለው የሚመለከተው የማግስት ማስርያ ቤት ለእነዚህ ሠራተኞች አበሉ ሊከፈል የሚገባ መሆኑን ሲወስን እና ይህም ማስረጃ ቀርቦ በባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ወይም እሱ በሚወክለው ሰው ሲፈቀድ ብቻ ነው፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 ማስረት የሚቀርብ ማስረጃ የአስቸጋሪ ሁኔታዉን ማጠን፣ ጉዳት ሊያደርስ የሚችልበትን የአካባቢ ሽፋን እንደ የርቀቱ የሚገልጽ፣ የስራ ሁኔታው ሊያደርስ የሚችለዉን የጉዳት ደረጃ ከፍተኛ፣ መካከለኛ ወይም አነስተኛ ብሎ በማየት የሚገልጽ መሆን አለበት፡፡

3. በስራ ሁኔታ አስቸጋሪነት ምክንያት የሚከፈል አበል ከገቢ ግብር ነፃ የሚሆነው አነስተኛ ጉዳት ለሚያስከትል የስራ ሁኔታ ከሠራተኛው የወር ደመወዝ ከ25%፣ መካከለኛ ጉዳት ለሚያስከትል የስራ

ሁኔታ ከሠራተኛው የወር ደመወዝ ከ40%፣ ከፍተኛ ጉዳት ለሚያስከትል የስራ ሁኔታ ከሠራተኛው የወር ደመወዝ ከ60% ባልበለጠ ማጠን ብቻ ነው፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 የተደነገገው ቢኖርም የጉዳቱን ደረጃ የሚለይ ማስረጃ ያልቀረበ ከሆነ ወይም የጉዳት ደረጃውን ማላካት የማይቻል ከሆነ ከተቀጣሪው የወር ደመወዝ ከ25% ባልበለጠ ማጠን ከገቢ ግብር ነጻ ይደረጋል፡፡

## 9. በማንኛውም ማለከ ለላቀ የስራ ክንውን የሚሰጥ ሽልማት፣

1. በአዋጁ አንቀጽ 65(1) ለላቀ የስራ ክንውን የሚሰጥ ሽልማት ከገቢ ግብር ነፃ ሊደረግ የሚቻለው በሚከተሉት ሁኔታዎች የተሰጠ ሽልማት ሲሆን ብቻ ነው፡

ሀ. አንድን ቴክኖሎጂ በማሻሻል፣ አዲስ የፈጠራ ሥራ በማሥራት ወይም ወጪን ለመቀነስ የሚያስችል አሰራር ስራ ላይ በማዋል የሚሰጥ ሽልማት፣

ለ. በአለም አቀፍ ደረጃ በሚደረግ ወድድር አገርን ወክሎ ወይም በአገር አቀፍ ደረጃ በሕግ በተቋቋመ የሽልማት ድርጅት በሚደረግ ማንኛውም ወድድር የሚሰጥ ሽልማት፣

ሐ. በፌደራል፣ በክልል፣ በአዲስ አበባ ከተማ ወይም በድሬዳዋ አስተዳደር መንግስት የላቀ የስራ ክንውን ለፈፀመ ማንኛውም ግለሰብ ወይም ድርጅት የሚሰጥ ማንኛውም ሽልማት ሲሆን ነው፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1/ሀ/ የተመለከተው ሽልማት ከገቢ ግብር ነፃ ሊሆን የሚቻለው ከፈጠራ ሥራው ጋር ግንኙነት ያለው አግባብነት ባለው የመንግስት አካል ለፈጠራው ሥራ እውቅና የተሰጠው ወይም የፈጠራ መብት ያገኘ ሲሆን ነው፡፡

## 10. ለተቀጣሪ በነፃ የሚቀርብ ምግብ እና ማጠጥ

1. በማዕድን ማውጣት፣ በማኑፋክቸሪንግ፣ በግብርናና ሆርቲካልቸር እንዲሁም በሆቴሎች፣ ሬስቶራንቶች እና የምግብ አገልግሎት ሥራ ላይ የተሰማሩ ቀጣሪ ለተቀጣሪዎቹ በነፃ የሚያቀርበው ምግብ እና ማጠጥ ከገቢ ግብር ነፃ ሊደረግ የሚቻለው ቀጣሪው ያለልዩነት ለሁሉም ተቀጣሪዎች ነፃ የምግብና ማጠጥ አገልግሎት የሚያቀርብ መሆኑ የተረጋገጠበት ሰነድ ወይም የሰራተኛ ማህበር ሚዎች ከድርጅቱ ጋር የተስማማበት ሰነድ ሲቀርብ ብቻ ነው፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 ማለረት ከግብር ነፃ የሚደረገው ማጠጥ የአልኮል ይዘት ያለው ሊሆን አይችልም፡፡

# ክፍል ሶስት
# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 11. በልዩነት ስለሚከፈል ግብር

ቀጣሪው በዚህ መመሪያ ከተወሰነው ገንዘብ በላይ ለተቀጣሪው የሚከፍል ከሆነ በብልጫ በተከፈለው ገንዘብ ላይ ግብር ይከፈልበታል፡፡

## 12. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

አዋጁ ስራ ላይ ከዋለ በኃላ በእንጥልጥል ያሉ እና ወሳኔ ያላገኙ ጉዳዮች በዚህ መመሪያ መሰረት ወሳኔ ያገኛሉ፡፡

## 13. የተሻረ መመሪያ

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት መመሪያዎች ተሽረው በዚህ መመሪያ ተተክተዋል፡፡

1. የኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣን ያወጣው የግብር ነፃ መብቶች መመሪያ ቁጥር 21/2001 እና መመሪያ ቁጥር 102/2007
2. በግብርና ልማት፣ ሆርቲካልቸር፣ በማእድንና ነዳጅ ቁፋሮ እና በፋብሪካ ደረጃ በማምረት ተግባር ላይ የተሰማሩ ድርጅቶች ለሰራተኞቻቸው የሚያቀርቡት ነፃ የምግብ አገልግሎት ከገቢ ግብር ነፃ ለማድረግ የወጡ ሰርኩላር ደብዳቤዎች

## 14. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከሚያዝያ 1 ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ መጋቢት 20 ቀን 2011 ዓ.ም**

**አህመድ ሺዴ**
**የገንዘብ ሚኒስትር**